# የገመድ ፓምፕ ብድር መመሪያ

## Operation Procedure for the Rope Pump Credit Scheme



Better Life with Rope Pump

የተሻለ ኑሮ በገመድ ፓምፕ


OMFI
ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም (አ.ማ)
OMO MICRO FINANCE INSTITUTION (S.C)

JICA

# የገመድ ፓምፕ ብድር መመሪያ

**ማዉጫ**


1. የገመድ ፓምፕ የብድር አገልግሎት
2. የብደር አገልግሎት አሠራር
3. የባለድርሻ አካላት ኃላፊነትና ሚና
4. ገመድ ፓምፕ


## Operation Procedure for the Rope Pump Credit Scheme


1st Edition: June 2014
2nd Edition: March 2016
Prepared by JICA WAS-RoPSS / WIDB and OMFI

## 1. የገመድ ፓምፕ የብድር አገልግሎት

**ዓላማ**

የገመድ ፓምፕን በማሰራጨት የገጠር መጠጥ ዉሃን አቅርቦት ለማሻሻል በአሞ ማ/ፋ/ ተቋም ዉስጥ ህጋዊነት ያለዉ የብድር አገልግሎት ማዕቀፍ መመሥረት፡፡

**ተጠቃሚዎች**

የገመድ ፓምፕ ለመግዛትና ለማስተከል ፍላጎት ያላቸው

**የብድሩ መጠን**

የተጣራ ብር እስከ 5,000 ሆኖም ግን እንደገበያው ሁኔታ በየጊዜው የሚወሰን ወይም የሚታደስ ሆኖ ውሳኔው ግን በክልል ደረጃ በሁለቱ ፈራሚ አካላት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

**የብድር ጊዜ**

1 እስከ 2 ዓመት

**የወለድ መጠን**

10% ዓመታዊ ወለድ መጠን እና 2% የአገልግሎት ክፊያ

### ቅጣት

የገመድ ፓምፕ ተጠቃሚ በወቅቱ ወይም በግዜ መክፈል ባይችል በአሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም የገጠር ብድር መመሪያ መሰረት ቅጣት የሚጣልበት ይሆናል፡፡

እጅ በእጅ ክፍያ የሚከፍሉ ወይም የሚፈፅሙ የገመድ ፓምፕ ተጠቃሚዎች ከወለድ ነፃ ይሆናሉ፡፡ ነገር ግን 2% የአገልግሎት ክፍያ የሚከፍሉ ይሆናሉ፡፡

**ተያዥ ንብረት (Collateral)** (ሁለት አማራጮች መጠቀም ይቻላል)

- ቢያንስ ግማሽ ሄክታር መሬት ያለዉ
- ለገመድ ፓምፕ ብድር የሚያበቃ ንብረት እንዳለዉ ከቀበሌ አስተዳደር ደብዳቤ ማቅረብ የሚችል እና ለብድር ዋስትና የሚሆን የይዞታ ማረጋጋጫ ማቅረብ የሚችል፡፡
- የጠለፉ ወይም (የቡድን) ዋስትና
- የደሞዝ ዋስትና ማቅረብ የሚችል
- ተቋማዊ ሌሎች የዋስትና አማራጭ ማቅረብ የሚችል

## 2. የብድር አገልግሎት አሠራር (አካሄድ)

የብድር አገልግሎት 5 ደረጃዎች አሉት፡፡እነሱም በተመሣሣይ ጊዜና በተደጋጋሚ የሚፈፀሙ ናቸዉ፡፡እነሱም የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

1.ማስተዋወቅ

2. ተጠቃሚን መምረጥ

3. ገመድፓምፕን መትከል

4. ክፍያ እና ገመድፓምፕ መጠቀም እንደ አስፈላጊነቱ መጠገን

5. ማስፋፋት




ምስል1: የብድር አገልግሎት አሠራር

የሚከተሉት ደግሞ የእያንዳንዱ ደረጃዎች ዝርዝር መግለጫዎች ናቸዉ፡፡

## 1. ማስተዋወቅ

የገመድ ፓምፕን በማስተዋወቅ ረገድ የሚከተሉት 3

ዋና ዋና ተግባራት እንዲፈፀሙ ይመከራል፡፡

1-1.የገመድ ፓምፕ ብድር አገልግሎት ግንዛቤ ማስጨበጥ

1-2.ገመድ ፓምፕን ከብድር አገልግሎት ጋር ማስተዋወቅ


1-3. አመልካችን መመዝገብ

**1-1.የገመድ ፓምፕ ብድር አገልግሎት ላይ ግንዛቤ ማስጨበጥ**

የኦሞ ማይክሮ-ፋይናንስ ተቋም ዋና መ/ቤት ከደቡብ/ብ/ብ/ህ/ክልላዊ መንግሥት ዉሃ ሀብት ቢሮ ጋር በመሆን ለኦሞ ማይክሮ-ፋይናንስ ተቋም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ንዑስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለቁጠባና ብድር ኤክስቴሽን ኤጀንቶች እንዲሁም ለወረዳ ዉሃ ጽ/ቤቶች የገመድ ፓምፕ ብድር አገልግሎት በተመለከተ ግንዛቤ ያስጨብጣሉ፡፡

ስለብድር ጥሩ የሆነ ዕዉቀት እንዲኖራቸዉና በመስክ ደረጃም በአግባቡ እንዲተገብሩ እገዛ ያደርጋሉ፡ ፡

**1-2.የገመድ ፓምፑን ከብደር አገልግሎት ጋር ማስተዋወቅ**




## 1.3 አመላካችኞን መመዝገብ

የኤክስቴሽን ወኪሎች (የአሞ ማ/ፋ/ቁ/ብ/ኤ ኤጀንቶች፣ የጤና እንዲሁም የግብርና ልማት) በየቀበሌያቱ ያሉትን የገመድ ፓምፑን ለመጠቀም ፍላጎት ያላቸዉን እጩ ተጠቃሚዎችን ይመዘግባሉ፡፡ምዝገባዉን እንዳጠናቀቁ በቀበሌያቸዉ በኩል ለወረዳ ዉሃ ጽ/ቤት ያስተላልፋሉ፡፡ ምዝገባዉ የሚከተለዉን መረጃዎች ማካተት አለበት

- የጉድጓዱን ባለቤት ሙሉ ስም
- የስልክ ቁጥር
- የቀበሌዉና የጎጥ ስም
- የጉድጓዱን መረጃ

## 2. ለተከላ መምረጥ

ከመረጣ እስከ ተከላ ያለዉ የሥራ ቅደም ተከተል እደሚከተለዉ ይሆናል፡፡




**ደረጃ1 የገመድ ፓምፕ ፈላጊዎች ዝርዝር (ከላይ 1.3 የአመላካቾች ምዝገባ ሥር ገጽ- ላይ እንደ ተገለፀ)**

| | |
|---|---|
| 【ዋና ዋና ተግባራት】 | 1. ጉድጓድ ያላቸዉና የገመድ ፓምፕን ለመግዛት ፍላጎት ያላቸዉን አባወራና እማወራ ዝርዝር ማዘጋጀት፡፡<br>2. ዝርዝሩን ለቀበሌ WaSH ቡድን/ ግብረ-ሃይል ማቅረብ፡፡ |
| 【ፈፃሚ አካል】 | የኤክስቴሽን ሠራተኞች (የአሞ ቁጠባና ብድር ኤክስቴሽን ኤጀንቶች የጤና ኤክስቴሽንና የግብርና ልማት ኤክስቴሽን ኤጀንቶችን ወ.ዘ.ተ) |
| 【ማሳሰቢያ】 | በእርግጥ ሥራው በሚጀመርበት ጊዜ የወረዳዉ ዉሃ ጽ/ቤትና ወረዳ መስተዳድር እገዛ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ |

## ደረጃ2 በቀበሌ "WaSH" ቡድን ማጣሪያ ማካሄድ

| | | |
|---|---|---|
| 【ዋና ዋና ትግባራት】 | 1. | የቀበሌ "WaSH" ቡድን /ግብረ ሀይል በአመልካቹ ሁኔታ ላይ በመወያየት አመልካቹ ለብድሩ አገልግሎት ብቁ መሆኑን እንዲሁም አንዳንድ ሙያዊ ሁኔታዎችን ያጣራሉ፡፡ |
| | 2. | የቀበሌ "WaSH'ቡድን /ግብረ ሀይል ያጣራውን ለወረዳ ዉሃ ጽ/ቤት /የውሃ ሀብት ቢሮ/ ሙያዊ ማጣሪያ እንዲደረግ ያስተላልፋሉ፡፡ |
| 【ፈፃሚአካል】 | | የቀበሌ "WaSH"ቡድን /ግብረሀይል |

## ደረጃ3 ሙያዊ ዳሰሳ ማካሄድ (ማጣራት)

| | | |
|---|---|---|
| 【ዋናዋናተግባራት】 | 1. | በደረጃ1 ላይ በተጠቀሰዉ ዝርዝር መሠረት የወረዳው ውሃ ጽ/ቤት/ የውሃ ሀብት ቢሮ የጉድጓዱን ለገመድፓምፕ ተስማሚነት ሙያዊ ማጣሪያ ያካሄዳሉ፡፡ |
| | 2. | የወረዳዉ ውሃ ሙያዊ ማጣሪያ ፎርሙን የቱቦውን ዓይነት /size/ ይወስናል አማራጮችን ያቀርባሉ፡፡ |
| | 3. | ሙያዊ ማጣሪያ ካደረገ በኋላ ለአሞ ማይክሮ-ፋይናንስ ተቋም ያስተላልፋል፡፡ |
| 【ፈፃሚአካል】 | | ወረዳ ውሃ ቢሮ |
| 【ማሳሰቢያ】 | | የዳሰሳ ቅጽ /ሡንጠረዥ ፎርም ለብቻው ተዘጋጅተዋል |

### ተጨማሪ የሙያዊ ዳሰሳ (ማጣሪያ )መመዘኛ ነጥቦች

ገመድ ፓምፑ ጥልቀታቸዉ መለስተኛ ለሆኑ ጉድጓዶች በመሆኑ የጉድጓዱ ሁኔታ ከሚከተሉት ነጥቦች አኳያ መታየት ይኖርባቸዋል ፡፡

1 የጉድጓዱ ጥልቀት ከ 35 ሜትር ያነሰ መሆን አለበት፡፡
2. የጉድጓዱ አፍ ዲያሜትር 1.2 ሜትር መብለጥ የለበትም፡፡
3. ጉድጓዱ በበጋ ጊዜ የሚደርቅ መሆን የለበትም፡፡
4. ጉድጓዱ ከሽንት ቤት ቢያንስ 30 ሜትር መራቅ አለበት፡፡
5. ጉድጓዱ ከሽንት ቤት በላይኛዉ በኩል (up stream) መሆን አለበት፡፤
6. የጉድጓዱ ባለቤት ዉሃዉን ለተለያየ ጥቅም (ለመጠጥ ፤ለመስኖ ፤ለእንስሳት ማጠጫ ለማጠቢያነት ወ.ዘ.ተ) እንዲጠቀም ይበረታታል፡፡
7. ጉድጓዱ ከማንኛዉም የቆሻሻ ምንጮች ነፃ መሆን አለበት፡፡
8. የጉድጓዱ ባለቤት በጉድጓዱን ዙርያ አጥር ለማጠር ፍቃደኛ መሆን አለበት፡፡
9. የጉድጓዱ ባለቤት ዉሃዉን ለመጠጥ በሚጠቀምበት ጊዜ ለዉሃዉ ጥራት ሃላፊነት መዉሰድ አለበት፡፡

**ደረጃ4 የአሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ማጣሪያ ( ዳሰሳ)**



【ዋና ዋና ተግባራት】

1. አመልካቹ ከዚህ በፊት ብድር ላይ ያለዉን ልምድና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ጉዳዮች አሞ ማይክሮ-ፋይናንስ ተቋም ያጣራል፡፡
2. የአሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ባለሙያዎች የአመላካች ቤት ድረስ በመሄድ ከብድር መመዘኛ ነጥቦች አኳያ ዳሰሳ ያደርጋሉ፡፡
3. አሞ ቁጠባ ብድር ተቋም አመልካች ለብድሩ ብቁ መሆኑ ወይም አለመሆኑን ይወሰናል፡፡

【ፈፃሚአካል】 የአሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ንዑስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

【ማሳሰቢያ】 የመያዣ ንብረት (collateral) እና ሌሎች አስፈላጊ የብድር መመዘኛ ነጥቦች የመግባቢያዉ ሰነድ (MOU) ዉስጥ በዝርዝር ሰፍሯል፡፡

**ደረጃ 5 ለብድር አገልግሎቱ ማመልከቻ ማቅረብ**



【ዋና ዋና ተግባራት】

1. የአሞ ማይክሮ-ፋይናንስ ተቋም የቁ/ብ/ኤ/ኤጀንት አመልካቹን በማግኘት የብድሩን ማመልከቻ ቅጽ እንዲፈርም ያደርጋሉ

【ፈፃሚ አካል】 አሞ ማይክሮ-ፋይናንስ ተቋም የቁ/ብ/ኤ ኤጀንት

【ማሳሰቢያ】 የማመልከቻ ቅጹ ለብቻው ተዘጋጅተዋል

**ደረጃ 6 የብድር አከፋፈል ዕቅድ ማዘጋጀት**

【ዋና ዋና ተግባራት】

1. ማመልከቻዉንና የማጣሪያ ሂደቱን መሠረት በማድረግ የአሞ ማይክሮ ፋይናንስ ቁጠባና ብድር ኤክስቴሽን ኤጀንቶች እና ንዑስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የብድር አከፋፈል ዕቅድ ለእያንዳንዱ አመልካች ያዘጋጃሉ፡፡
2. በተዘጋጀዉ የብድር አከፋፈል ዕቅድ ላይ ከአመልካቾች ጋር ይወያያሉ፡፡

【ፈፃሚአካል】 የአሞ ቁጠባና ብድር ተቋም ንዑስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና የቁ/ብ/ኤ/ ኤጀንት

【ማሳሰቢያ】 አሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም የብድር አከፋፈል ዕቅዱን ሲያዘጋጅ የአመልካቹን የመክፈል ችሎታ እና የኑሮ ሁኔታ ወዘተ በማየት ለአባወራዉ (እማወራዉ) ሞቹ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

**ደረጃ 7 የብድር ስምምነት በተጠቃሚው፣ በውሃ ቢሮ እና በኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም መሀከል መፈራረም**



| | | |
|---|---|---|
| 【ዋና ተግባራት】 | ዋና | 1. የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም የቁ/ብ/ኤ ኤጀንቶች የብድሩ ተጠቃሚ፣ የቀበሌዉ አመራር እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ ባለድረሻ አካላት የብድር ስምምነቱን ይፈራረማሉ::<br>2. በዚሁ ጊዜ ተጠቃሚው ከውሃ ቢሮ ጋር ስምምነት ይፈራረማሉ:: |
| 【ፈፃሚ አካል】 | | የኦሞ ቁጠባና ብድር ኤክስቴሽን ኤጀንቶች |

**ደረጃ 8 የብድርተጠቃሚዎችንዝርዝርለወረዳዉዉሃ ጽ/ቤትማስተላለፍ**


| | | |
|---|---|---|
| 【ዋና ተግባራት】 | ዋና | 1. የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ንዑስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተፈረመ የብድር ስምምነት ሰነዶችን ያሰባስባል::<br>2. በስምምነቱ መሰረት የብድር ተጠቃሚዎችን ስም ዝርዝር ያዘጋጃል::<br>3. የገመድ ፓምፕ ብድር ተጠቃሚዎችን ስም ዝርዝር እና የውል ስምምነት በደብዳቤ ለወረዳዉ ውሃ ጽ/ቤት ያስተላልፋል:: የደብዳቤዉን ግልባጭ ለክልሉ ዉሃ ቢሮ ጽ/ቤት ያቀርባል:: |
| 【ፈፃሚ አካል】 | | የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ንዑስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት |

**ድረጃ 9 የገመድ ፓምፑን ማመቻቸት**

| | | |
|---|---|---|
| 【ዋና ተግባራት】 | ዋና | 1. የወረዳ ውሃ ጽ/ቤት በደብዳቤ የተቀበለውን የተመቃሚ ዝርዝር ውል መሰረት የገመድ ፓምፕ ስፔስፍኬሽን እና እቃዎችን ያረጋግጣል::<br>2. 2 የወረዳ ውሃ ጽ/ቤት የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ንዑስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የማረጋገጫ ደብዳቤ ይልካል::<br>3. የወረዳ ውሃ ጽ/ቤት ገመድፓምፑን ያቀርባል::<br>4. የገመድ ፓምፑ እና ተያያዥ ዕቃዎች በተለያዩ ደረጃዎች ካሉ አምራቾች እና የአከባቢ ባለሙያዎች ማግኘት ይቻላል:: |

## ደረጃ 10 የፓምፕ ተከላ

| | |
|---|---|
| 【ዋና ዋና ተግባራት】 | ተጠቃሚዎች በአካባቢያቸዉ የሚገኙትን የሰለጠኑ የገመድ ፓምፕ ተካዮች ጋር በመነጋገር የፓምፑ ተከላ እንዲጀምር ይደረጋል፡፡ |
| 【ፈፃሚ አካል】 | የሰለጠኑ የአካባቢዉ ባለሙያዎች |



## የገመድ ፓምፑ ኦፔሬሽንና ጥገናና የብድር ክፍያ፡

የገመድ ፓምፕ ጥገናም ሆነ የብድር ክፍያዉ በየጊዜዉ የሚፈፀሙ ተግባራት ናቸዉ፡፡


**ኦፔሬሽንና ጥገና**



- ★ ለጥገና ሥራ ዋናዉን ሀላፊነት የሚወስዱት ተጠቃሚዎች ናቸዉ፡፡
- ★ የገመድ ፓምፑ ሁልጊዜ እንዲሰራ ለማረጋገጥ የወረዳ ዉሃ ጽ/ቤት በየጊዜዉ ክትትል ያደርጋል ፡፡
- ★ ቀለል ያሉ ጥገናዎች በተጠቃሚዉ ወይም በሰለጠኑ የአከባቢ ባለሙያዎች ይሆናል፡፡
- ★ ከበድ ያሉ ጥገናዎች የሚሰሩት በሰለጠኑ የአከባቢዉ ባለሙያ ወይንም በገመድ ፓምፕ አምራቾች ይሆናል፡፡

**የብድር አመላለስ**

- ★ የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ የ/ቁ/ብ/ኤ/ኤጀንቶች የብድር ክፍያዉን በተቀመጠዉ እቅድ መሠረት ይሰበስባሉ፡፡
- ★ የኦሞ ማይክሮ-ፋይናንስ የ/ቁ/ብ/ኤ/ኤጀንቶች የሰበሰቡትን ክፍያ ለንዑስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቢበዛ በ5 ቀን ሪፖርት ያደርጋል፡፡
- ★ የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ንዑስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የገመድ ፓምፕ የብድር ሁኔታን የሚገልፅ ሪፖርት በአንድ ወር ለቅ/ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡



## 3. የባለድርሻ አካላት ኃላፊነትና ሚና

| | የሥራዉ አይነት | በክልልደረጃ | | በወረዳደረጃ | | | ቀበሌደረጃ | | ተጠቃሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አሞ ማይክሮ | ዉሃ ቢሮ/ | አሞ ንዑስ ቅርንጫፍ | ወረዳ አስተዳደር | ወረዳ WaSH ቡድን | አሞ ማይክሮ የቁ/ብ/ኤ/ኤጀንቶች | ቀበሌ WaSH ቡድን | |
| 1 | የገመድ ፓምፕ ብድር ላይ ግንዛቤ መስጠት | ☆ | ☆ | ○ | | ○ | ○ | | |
| 2 | የገመድ ፓምፕን ከብድር ጋር ማስተዋወቅ | ○ | ◎ | ☆ | ☆ | ☆ | ☆ | ☆ | |
| 3 | የማመልከቻ ቅጽ ማከፋፈል | ◎ | | ☆ | | | ☆ | | |
| 4 | አመልካቾችን ማጣራት | ◎ | ○ | ☆ | ◎ | ○ | ☆ | ☆ | |
| 5 | የብድር ክፊያ እቅድ | ○ | ○ | ☆ | ◎ | ◎ | ☆ | ◎ | |
| 6 | የብድር ስምምነት መፈረም | ◎ | | ☆ | | | ☆ | ☆ | ☆ |
| 7 | የገመድ ፓምፕ ለማቅረብ ዉል ፊርማ | | ☆ | | | ○ | | ○ | ☆ |
| 8 | የተጠቃሚዎች ዝርዝር | ☆ | | ☆ | | | ◎ | | |
| 9 | የገመድ ፓምፕ ተከላ | | ☆ | ○ | ○ | ◎ | ○ | ◎ | ☆ |
| 10 | የገመድ ፓምፕ መሥራትና የጥገና ሁኔታ | | ◎ | ◎ | | ☆ | ◎ | ☆ | ☆ |
| 11 | የብድር ክፊያ | ◎ | ○ | ☆ | ◎ | ○ | ☆ | ☆ | ☆ |
| 12 | ሪፖረትና መዝገብ አያያዝ | ☆ | ☆ | ☆ | ◎ | ◎ | ☆ | ◎ | ○ |
| 13 | ፕሮግራሙን ማስፋፋት | ☆ | ☆ | ☆ | ☆ | ☆ | ☆ | ☆ | |

☆ ዋና ተግባሪ ◎ የተግባርተካፋይ ○ድጋፊ

## 4. ገመድ ፓምፕ

- ✧ የገመድ ፓምፕ በአነስተኛ ዋጋ ውሃን ከጉድጓድ ለማዉጣት የሚረዳ መሳሪያ ነዉ::
- ✧ የገመድ ፓምፕ ተጠቃሚ እራሱ በራሱ ወጪ ሊገዛዉ የሚችል መሳሪያ ነዉ::
- ✧ በመሆኑም መንግስት የገመድ ፓምፕን በብሔራዊ ዕቅድ ውስጥ አካቷል::



ገመድፓምፕ

OMO MICRO FINANCE INSTITUTION (S.C)